# የባፕቲስት
# አቋመ
# እምነት
# 1689

ተጨማሪ ማብራሪያዎች

በዶ/ር ፒተር ማስተርስ

# የባፕቲስት አቋመ እምነት
# 1689

ወይንም
ሁለተኛው የለንደን አቋመ እምነት ከመጽሐፍ
ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ጋር

ተጨማሪ ማብራሪያዎች
በዶ/ር ፒተር ማስተርስ

ትርጉም
ፓስተር ኃይለልዑል ተፈራ

THE WAKEMAN TRUST, LONDON

# የባፕቲስት አቋመ እምነት 1689

© 1981 ይህ የተሻሻለው እትም እና ተጨማሪ ማብራሪያዎች በዶ/ር ፒተር ማስተርስ የተደረጉ ናቸው::

የመጀመሪያው እትመት 1981

ሰባተኛው እትመት በ2006

የመጀመሪያው የአማርኛ እትም 2007

THE WAKEMAN TRUST
[Wakeman Trust is a UK Registered Charity]

UK Registered Office
38 Walcot Square
London SE11 4TZ

US Office
300 Artino Drive
Oberlin, OH 44074-1263

Website: www.wakemantrust.org

ISBN 978 - 1 - 870855 - 58 - 7

የእርማት ንባብ ደምሰው ሽፈራው

የሽፋን ዲዛይን ቬራ ሉን

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ሆነ በሙሉ ያለ አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ በማናቸውም መንገድ ማባዛት በሕግ የተከለከለ ነው::

Printed by Rehoboth Printing Enterprise, Addis Ababa, Ethiopia
በርሆቦት ማተሚያ ድርጅት ታተመ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

# መቅድም በስፐርጅዮን

*(በ1855 የባፕቲስት የእምነት አቋም መጽሐፍ በስፐርጂዮን እንደገና እንዲታተም ተደረገ። በቅድሚያም ለእራሱ ማህበረ ምዕመን ጠቀሜታ ታስቦ ነበር። የስፐርጂዮንም የመግቢያ ቃላት የዚህን አስደናቂ የሆነ ዶክትሪን ቃላት ዋጋ በትክክል ያንፀባረቁ ነበሩ)*

ይህ ጥንታዊ ሰነድ በእኛ መካከል በጣም የምናምንባቸውን ነገሮች በትክክል የሚገልፅ በጣም ፍፁም የሆነ ምሳሌ ነው። በሥላሴ እግዚአብሔር አስደናቂ ጥበቃ እጅ አማካኝነት ለከበረው ለእኛ የወንጌል እውነት ታማኞች ሆነን ተጠብቀናል፣ በእነሱም ለዘላለም ለመፅናት እና ለመናር በቆራጥነት መወሰናችን ይሰማናል።

ይህ ትንሽ መጽሐፍ የተሰጠው እንደ ገገር ሕግ፣ ወይንም እንደ እምነት ደንብ በመሆን እናንተ እንድትታሰሩበት አይደለም፣ ነገር ግን በአወዛጋቢ ወቅት እንዲረዳችሁ፣ እንደ እምነት ማረጋገጫ እንዲሆንላችሁ እንዲሁም በፅድቅ ላለው ሕይወት እንድትገነቡበት ነው። ወጣት ለሆኑት የቤተ ክርስቲያናችን አባላት፣ አቅጣጫ መሪ የሚሆን የሥነ-መለኮት ትምህርት በዚህ ውስጥ አለላቸው፣ እንዲሁም በውስጡ ባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ የጥቅስ ማስረጃዎች አማካኝነት በእነሱ ውስጥ ስላለው ተስፋ መልስን ለመስጠት ዝግጁዎች ይሆኑበታል።

በእምነታችሁ አትፈሩ፣ እምነታችሁም ጥንት የተሰውት የሰማዕታት፣ እምነታቸውን በይፋ የገለፁት የተሃድሶ መሪዎችና የቅዱሳን ወንጌል እንደሆነ አስታውሱ። ከሁሉም ይበልጥ ደግሞ የገሃነም ደጃፎች የማይቋቋሙት የእግዚአብሔር እውነት ነው። የእናንተ ሕይወት እምነታችሁን ያክብረው፣ ምሳሌነታችሁ የእምነት መግለጫችሁን የሚያስመሰክር ይሁን። ከሁሉም ይልቅ በክርስቶስ ኢየሱስ ኑሩ፣ በእሱም ተራመዱ፣ በእሱ ላልተረጋገጠና በመንፈስ ቅዱስም ላልተመሠረተ ትምህርት ሥፍራ አትስጡ። እንደ ሕይወት ካርታ ከተዘጋጀላችሁ ከዚህ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በጣም ተጣበቁ።

በብዛት ለላቲን ቃል ምንጫቸው የቀረቡ ስለነበሩ፤ በመጀመሪያው ስራ ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሰጡ ለመሆኑ በጣም ግልፅ ይመስላል:: ለዚህም የሚሆን ማስረጃ ባለበት ቦታ ተመሳሳዩና በእምነት አቋሙ አቀናባሪዎች የታቀደውን ሐሳብ የሚያስተላልፈው ቃል ተመርጧል:: እንደተለየ ሆኖ ምዕራፍ 20 ቁጥር 3 በመጀመሪያው ሁኔታው አብሮት ከተከተለው መስተካከል ጋር ተጠቅሷል:: ምክንያቱም ያ አንቀፅ በጣም አሻሚና ከተ ለመደው የበለጠ ማብራሪያን ስለሚጠይቅ ነው::

ይህ ማሻሻያ ከመጀመሪያው ጋር የተጠጋጋ፣ ታማኝ የሆነ፤ ፍትሐዊ የሆነን ሥራ ስሜት ይሰጣል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል፣ ይህም በተገቢው ሁኔታ ለመጪው ትውልድ ያለውን የበለፀገ ከፍተኛ ዋጋ በማስተላለፍ እንዲያገለግል ነው::

# የ1689 የእምነት አቋም ድማሬ

በፓርቲኩላር ባፕቲስቶች [Particular Baptists] በመጀመሪያ ተዘጋጅቶ የወጣው የእምነት አቋም የታየው በ1644 ማለትም፣ የዌስትሚኒስተር የእምነት አቋም ከመውጣቱ በፊት ነበር:: አቋመ እምነቱም በጥብቅ ይገልፅ የነበረው ልብስ የለበሱ ሰዎችን የጥልቀት ጥምቀትንና እንዲሁም የፓርቲኩላር ባፕቲስቶችን [Particular Baptists] ከጀነራል ባፕቲስቶች [General Baptists] የሚለዩበትን ነጥቦች ማለትም የአማኞችን ምርጫ፣ የተወሰኑትን መዳን፣ የሰው ፈቃድ የወደቀ ሁኔታን እና የቅዱሳን የዘላለም ዋስትናን ስለጨመረ ነበር:: የለንደን የእምነት አቋምም ተብሎ በመታወቅ በ1651 እንደገና ተሻሽሎ ነበር:: (በዚህም ጊዜ «ኳይከርስ» የሚባለውን እና መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም «የውስጥ ብርሃን» ያስፈልጋል የሚለውን እንቅስቃሴ፣ በአሁኑ ጊዜ «ጥልቅ ሕይወት» [deeper life] ወደ መባል የተቀየረውን ለመቃወም የሚያስችሉ አንቀፆችን በመጨመር ነበር)::

በ1643 ሎንግ ፓርላማው [Long Parliament]* (የአንግሊካን ቤተ ክርስትያንን መዋቅራዊ አደረጃጀት ካፈረሰ በኋላ) በዌስትሚኒስተር የእግዚአብሔር ሰዎችን ጉባኤ በመጥራት የቤተክርስትያንን አስተምህሮ እና አስተዳደርን እንዲያዘጋጁ አዘዘ:: በዚያ በጣም ልዩ ችሎታ በነበራቸው

* Long Parliament:- በህዳር 3 1640 ተጀምሮ ከ13 ዓመታት በኋላ ሚያዝያ 20 1653 የተበተነውና ረጅም ዘመን የፈጀውን የእንግሊዝ ፓርላማን ስብሰባ የሚያሳይ ስያሜ ነው::

# ሠላሳ ሁለቱ የእምነት አንቀፆች

## ማውጫ


1. ቅዱሳት መጻሕፍት 9
2. እግዚአብሔርና ቅዱስ ሥላሴ 14
3. የእግዚአብሔር ድንጋጌ 16
4. ፍጥረት 19
5. መለኮታዊ ቸርነት 20
6. የሰው ውድቀት ኃጢአትና ቅጣት 22
7. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን 24
8. የክርስቶስ አማላጅነት 25
9. ነፃ ፈቃድ 29
10. ብቁ ጥሪ 30
11. ፅድቅ 31
12. ልጅነት 33
13. ቅድስና 34
14. የሚያድን እምነት 35
15. ንስሐና ደኅንነት 36
16. መልካም ሥራ 38
17. የቅዱሳን ፅናት 40
18. የደኅንነት ማረጋገጫ 42
19. የእግዚአብሔር ሕግ 44
20. ወንጌልና ተፅዕኖው 47
21. የክርስትያን ነፃነትና የሕሊና ነፃነት 48
22. አምልኮና የሰንበት ቀን 50
23. ሕጋዊ መሐላዎችና ስለቶች 52
24. የመንግስት ባለሥልጣናት 54
25. ጋብቻ 55
26. ቤተክርስትያን 56
27. የቅዱሳን ኅብረት 62
28. ጥምቀትና የጌታ እራት 63
29. ጥምቀት 63
30. የጌታ እራት 64
31. ከሞት ከትንሳኤ በኋላ የሰው ሁኔታ 66
32. የመጨረሻው ፍርድ 67

4. የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን መታመን ያለበት «የእኛን ታዛዥነት የሚጠይቀው» በማንኛውም ሰው ወይም ቤተክርስትያን ምስክርነት ላይ ተመሥርቶ አይደለም ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ በጸሐፊው በእግዚአብሔር ላይ ነው:: ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ተቀባይነት (ታዛዥነት) ማግኘት አለበት[7]::

(በሌላ ለነጋገር እግዚአብሔር በሚናገርበት ጊዜ የእሱ ትዕዛዛትና ትምህርቶች ጥያቄ ውስጥ ሊገቡ አይገባም:: ማመን ወይም መቀበል ያለብን አገልጋዩ ትምህርቱ ተገቢና አስፈላጊ ነው ስላለን ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ከመሆኑ የተነሳ ነው:: የሮም ካቶሊክ ቤተክርስትያን መጽሐፍ ቅዱስን እንደመረመረችውና ዋስትና እንደሰጠችው፣ እንዲሁም ቤተክርስትያኒቷ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም ስልጣን እንዳላት ትናገራለች:: ነገር ግን በመጀመሪያ የመጣው፣ በእግዚአብሔር የተሰጠው፣ እራሱን በራሱ የሚያረጋግጠው እና ቤተክርስትያንን ሊገዛ የሚገባው ቃሉ ነው)::

7. 2ጴጥ. 1:19-21፣ 2ጢሞ. 3:16፣ 1ተሰ. 2:13፣ 1ዮሐ. 5:9::

5. በእግዚአብሔር ሕዝብ ምስክርነት ተነክተን ወይም ተገፋፍተን ለእግዚአብሔር ቃል ከፍተኛ የሆነ አክብሮት ወይም ግምት አግኝተን ይሆናል:: እንደዚሁም በቅዱሳት መጻሕፍት ባሕርይ ተነክተን ይሆናል ማለትም:-

(የይዘታቸው ሰማያዊነት፣ የአስተምህሯቸው ብቁነት (የትምህርታቸው ብቁነትና ኃይል)፣ የአቀራረባቸው ግርማ-ሞገስ፣ የአጠቃላይ ክፍሎቹ አንድ ወጥ መሆን (ያስምንም ግጭት የሁሉም መጻሕፍት መስማማት)፣ የሁሉም አጠቃላይ አድማስ ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ መሆኑ፤ ለሰው የመዳኛው መንገድ ይህ ብቻ እንደሆነ ሙሉ ገለፃን ማድረጉና ከሌሎች ወደር ከሌላቸው የከበሩ ባህርያቱና አጠቃላይ ፍፁምነቱ ጭምር ነው:: በነዚህ ሁሉ ማስረጃዎች መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ ከሁሉ የበለጠ እራሱ ያረጋግጣል)::

ይህ እንዲህ ቢሆንም በቃሉ ስህተት-አልባነት፤ እውነትነትና መለኮታዊ ስልጣን ላይ የኛ ሙሉ እምነትና እርግጠኝነት የተመሠረተው መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው ምስክርነትና በልባችን ውስጥ ባለው ቃሉ መሠረት በሚሠራው ውስጣዊ ሥራ የተነሳ ነው[8]::

8. ዮሐ. 16:13-14፣ 1ቆሮ. 2:10-12፣ 1ዮሐ. 2:20 ና 27::

6. የእግዚአብሔር ምክር በሙሉ (ዕቅድና ዓላማው) ስለ ሁሉም ነገሮች ለእራሱ ክብር አስፈላጊ በሆኑት የሰው ደኅንነት፣ እምነትና ሕይወት በግልጥነት ተቀምጠዋል ወይም በቅዱስ ቃሉ ውስጥ የግድ ይገኛሉ በነዚህም ላይ በማንኛውም ጊዜ በአዲስ የመንፈስ መገለጥ ወይም በሰዎች

አለመስማማቶች) ሁሉ ለመጨረሻ ውሳኔ ቤተክርስትያን እነሱን ማየት አለባት[15]::

ነገር ግን ለእግዚአብሔር ቃል መብትና ዝንባሌ ላላቸው፣ በእግዚአብሔ ርም ፍርሃት ውስጥ በመሆን እንዲያነቧቸውና[16] እንዲመረምሯቸው[17] ለታዘዙት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ እነዚህ የመጀመሪያ ቋንቋዎች የማይታወቁ ናቸው፤ በመሆኑም ቅዱሳት መጻሕፍት ሕዝቦች ሁሉ በመጡበት በአካባቢ ቋንቋቸው ሊተረጎሙ ይገባል[18]:: ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል በሁሉም ውስጥ በሙላት በመኖሩ ሰዎች እግዚአብሔ ር ሊቀበለው በሚፈልገው መንገድ ያመልኩታል፣ እንዲሁም ቃሉ በሚሰጠው በትዕግስትና በመፅናናት ተስፋ ይኖራቸዋል[19]::

14. ሮሜ 3:2፣ 15. ኢሳ. 8:20 16. ሐዋ. 15:15፣ 17. ዮሐ. 5:39፣
18. 1ቆሮ. 14:6. 9፣ 11-12፣ 24. 28፣ 19. ቆላ. 3:16::

9. የማይሳሳተው (ስህተት የሌለበት) የእግዚአብሔርን ቃል መፍቻው ሕግ እራሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ ስለዚህም የማንኛውንም የእግዚአብሔርን ቃል በተመለከተ የእውነተኛና የሙሉ ትርጉም ጥያቄ በሚነሳበት ጊዜ ሁሉ (ብዙ መልክ ሳይሆን ነገር ግን አንድ) የበለጠ ግልጥ አድርጎ በሚናገር ወይም በሚያሳይ በሌላ ክፍል ሊመረመር ያስፈልጋል::. (ይህም በዚያ አንፃር ለመረዳት ነው)[20]::

(«በብዙ መልክ ሳይሆን ነገር ግን አንድ» የሚለው ሐረግ የሚያመለክተ ው የእግዚአብሔር ቃል ዝም ብሎ የመጽሐፍት - ቤተመጽሐፍ፣ ወይም የጠቃሚ መጽሐፍት ስብስብ፣ ወይም «የመረዳቶች» ጥርቅም እንዳይደለ ነው:: እንደ እግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ያለምንም የእርስ በእርስ ቅራኔ ወይም መምታታት አንድ ወጥ የሆነ መልክት ያለው ነው:: ስለዚህም አንድን ክፍል ከሌላ ክፍል ጋር በማነናዘብ የሚደረግ የመተ ርጎም ልምድ የታመነ የመተርጎም መንገድ ወይም ዘዴ ነው)::

20. 2ጴጥ. 1:20-21፣ ሐዋ. 15:15-16::

10. ሃይማኖታዊ ውዝግቦችን ሁሉ ሊዳኝ (ሊፈርድ) የሚችል ከፍተኛው ዳኛ፣ እንዲሁም የጉባኤዎች፣ የእምነት መግለጫዎች፣ የጥንት ጸሐፊዎች አስተያየቶች፣ እንዲሁም የሰዎች ትምህርቶችና የግል መንፈሶች (የግል ፍልስፍናዎች) ሊመረመሩበት የሚገባ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከተሰጠው ከቅዱስ ቃሉ ውጭ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም:: እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል ዓረፍተ ነገር ውስጥ እናርፋለን (ስንረካበን) ምክንያቱም የእምነታችን የመጨረሻ መፍትሄ ያለው በመንፈሱ በተሰጠው

በእውነት ለሚፈልጉት ለእነዚያ ዋጋ የሚሰጥ[13]። እንዲሁም በተ መሳሳይ መንገድ በፍርዱ በጣም ፍትሃዊና አስፈሪ[14] (የማይበገር)፣ ኃጢአትን ሁሉ የሚጠላ[15]፤ እናም በደለኛውን በምንም መንገድ ንፁህ ነህ የማይል[16] ነው።

1. 1ቆሮ. 8:4-6፣ ዘዳ. 6:4፣ 2. ኤር. 10:10፣ ኢሳ. 48:12 3፣ ዘፀ. 3:14፣
4. ዮሐ. 4:24፣ 5. 1ጢሞ1:17፣ ዘዳ. 4:15-16፣ 6. ሚል. 3:6፣ 7. 1ነገስ. 8:27፣
ኤር. 23:23፣ 8. መዝ. 90:2፣ 9. ዘፍ. 17:1፣ 10. ኢሳ. 6:3፣ 11. መዝ. 115:3፣
ኢሳ. 46:10፣ 12. ምሳ. 16:4፣ ሮሜ. 11:36፣ 13. ዘፀ. 34:6-7፣ ዕብ. 11:6፣
14. ነህ. 9:32-33፣ 15. መዝ. 5:5-6፣ 16. ዘፀ. 34:7፣ ነህ. 1:2-3።

2. እግዚአብሔር ሕይወትን ሁሉ[17]፣ ክብርን[18]፣ መልካምነትን[19]፣ በ ረከትን፣ ከራሱና በራሱ ውስጥ ይዞ ሁሉን በመቻሉ ልዩ ነው፣ ይህም በሁለቱም መልክ ማለትም በራሱና ለራሱ ነው፣ የማንኛውንም የፈጠ ረውን ፍጡር ርዳታ አያስፈልገውም ወይም ከሌላው ምንም ክብርን ባለመውሰድ ነው[20]።

በአንፃሩ በእነሱ ውስጥ ለእነሱ እና በእነሱ ላይ የራሱን ክብር የገለጠው እራሱ እግዚአብሔር ነው። እሱ ብቻውን የሁሉ ነገር የሁሉ ሕልውና መፍለቂያ (ምንጭ) ነው፣ በመሆኑም ሁሉ ነገር ያለውና የሚንቀሳቀሰው በእሱ፣ ከእሱ፣ እና ለእሱ[21] (እሱ ነው የሰው ልጅ ሁሉ ፍፃሜ ያኘ እና ምንጭ) ነው።

እሱ በፍጥረት ሁሉ ላይ ደስ የሚለውን ማናቸውንም ነገር ሁሉ በእነሱ ላይ፣ በእነሱ ውስጥ ወይም ለእነሱ ለማድረግ ፍፁም ሙሉ የሆነ መለኮ ታዊ ሥልጣን አለው[22]።

በእሱ ዕይታ ሁሉ ነገር ግልጥና የተራቆተ ነው[23] የእሱ ዕውቀት የማይወሰን፣ የማይሳሳት፣ እናም በፍጡሩ ላይ ያልተወሰነ ነው። (እሱ ስለሆነው ነገር ለመረዳት በመላዕክት ወይም በሰዎች ሪፖርት ላይ አይደገፍም)።

ስለዚህም ለእሱ ምንም ነገር ድንገተኛ ወይም ያልታወቀ (በሁኔታ ከስተት ላይ የተመሠረተ) አይደለም[24]።

በምክሩ (በዕቅዶቹና በዓላማዎቹ) በሥራው እንዲሁም በትዕዛዛቶቹ ሁሉ እሱ በጣም ቅዱስ ነው[25]።

ለእሱ ከመላዕክትም ከሰዎችም አምልኮ አገልግሎት ሁሉ ወይም ታዛዥነት ይገባዋል[26]፣ እነሱ እንደ እሱ ፍጡራን እሱን የሚያስደስተውን ከእነሱ የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለፈጣሪያቸው ማድረግ አለባቸው።

ለማድነቅ፣ ምክንያትን ይሰጣል[20]፣ እንዲሁም ደግሞ ለትህትና፣ ለእውነተኛነት፣ ለብዙ መፅናናት ወንጌልን በቅንነት ለሚታዘዙ ሁሉ የማመስገኛ ምክንያትን ይሰጣል[21]::

18. 1ተሰ. 1:4-5፣ 2ጴጥ. 1:10 19፣ ኤፌ. 1:6፣ ሮሜ 11:33፣
20. ሮሜ 11:5-6 እና 20፣ ሉቃ. 10:20::

# 4. ፍጥረት

1. በመጀመሪያ እግዚአብሔር አብን ወልድንና መንፈስ ቅዱስን[1] ለዘላለም ክብሩ፣ ጥበቡ እና መልካምነቱ መገለጥ[2] ይህም ዓለምንና በውስጧ ያሉትን የሚታዩትንና የማይታዩትን ሁሉ በስድስት ቀናት[3] ውስጥ ለመፍጠር ደስ አሰኘው፣ እንዲሁም ሁሉም መልካም ነበር::

1. ዮሐ. 1:2-3፣ ዕብ. 1:2፣ ኢዮብ 26:13፣ 2. ሮሜ 1:20፣ 3. ቆላ. 1:16፣ ዘፍ. 1:31::

2. እግዚአብሔር ሌሎች ፍጥረታትን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ[4] ከማስተዋልና (ከስዋቂነት) ከሕያው ነፍስ ጋር ፈጠራቸው[5]፣ እነሱም ያንን ሕይወት ለእሱ ሲኖሩ ለተፈጠሩበት ለዚያ እንዲስማሙ አድርጎ ነው፣ በዚህም መሠረት:-

በእግዚአብሔር አምሳል በመሠራት በእውቀት በፅድቅ እና በእውነተኛ ቅድስና[6] የእግዚአብሔር ሕግ በልባቸው ተጽፎ[7] እናም ያንን ለማድረግ የሚያስችላቸውን ኃይል ይዘው ነው::

ነገር ግን ለመሳሳት በሚያስችል ሁኔታ ውስጥ በመኖር፣ ለራሳቸው ፈቃድ ነፃነት ተለቀው ነበር፣ ያም ሊለዋወጥ የሚችል[8] (ስማመዕ ነፃ ስለዚህም ያዕፀና በመሆን) ነበር::

4. ዘፍ. 1:27፣ 5. ዘፍ. 2:7፣ 6. መክብ. 7:29፣ ዘፍ. 1:26፣
7. ሮሜ 2:14-15፣ 8. ዘፍ. 3:6::

3. በልባቸው ከተፃፈው ሕግ ባሻገር መልካምንና ክፉውን ከምታስታውቀው ዛፍ[9] እንዳይበሉ ትዕዛዝን ተቀብለዋል:: ይህንን ትዕዛዝም እየፈፀሙ እያሉ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ሕብረት በጣም ደስተኞች ነበሩ እንደዚሁም በምድር ላይ ባሉት ፍጥረታት ሁሉ ላይ ገገርነት (ጌትነትና ተቆጣጣሪነት) ነበራቸው[10]::

9. ዘፍ. 2:17፣ 10. ዘፍ. 1:26፣ 28::

7. ሐዋ. 27:31 ና፥፥ ኢሳ. 55:10-11፣ 8. ሆሴ. 1:7፣ 9. ሮሜ. 4:19-21፣
10. ዳን. 3:27።

4. የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይሉ፣ የማይመረመረው ጥበቡና የማይወሰነው መልካምነቱ እስከአሁን ድረስ ራሳቸውን የገለጡት (ሙሉ በሙሉ የገለጡት) በእሱ ቸርነት ነው ያም የእሱ የተወሰነው ምክሩ (ቁርጠኛ ፅ ቀዱ) እስከ መጀመሪያው ውድቀት ድረስ እንኳን ተዘርግቷል እንዲሁም ለመላእክትም ለሰዎችም ሌሎችም የኃጢአት ሥራዎችም ጭምር[11]።

ይህም ዝም ብሎ በባዶ ፈቃደኛነት ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን በፈቃድ መልክ እሱ ባካተተው በጣም ኃይለኛና ጥበበኛ ወሰን እንዲሁም በሌሎች ኃጢአትን የመቆጣጠሪያና የማገጃ መንገዶች ጭምር ነው[12]። እነዚህም የተለያዩ ማገጃዎች በእግዚአብሔር የታቀዱት የእሱን በጣም ቅዱስ የሆኑትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ነው[13]።

ነገር ግን በእነዚህ ሁሉ ጉዳዮች የመላዕክትም ሆነ የሰዎች፣ የሁሉቱም ኃጢአተኛነት የመጣው ከእነርሱ ከራሳቸው ብቻ ነው እንጂ ሙሉ በሙሉ ቅዱስ እና ፃድቅ ከሆነውና፣ የኃጢአት ጀማሪና ተቀባይ በጭራሽ ሊሆን ከማይችለው ከእግዚአብሔር አይደለም[14]።

11. ሮሜ 11:32-34፣ 2ሳሙ. 24:1፣ 1ዜና 21:1፣ 12. 2ነገ. 19:28፣ መዝ. 76:10፣
13. ዘፍጥ. 50:20፣ ኢሳ. 10:6፣ 7 ና 12፣ 14. መዝ. 50:21፣ 1ዮሐ. 2:16።

5. በጣም ጥበበኛ፣ ፃድቅ፣ እና ባለፀጋው እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ልጆቹን ለራሳቸው የተበላሸ ልብ ኃጢአተኝነትና ለተለያዩ ፈተናዎች ለጊዜ ው ይተዋቸዋል ይህም ለሠሩዋቸው ኃጢአቶች ቅጣትን ለመቅጣት፣ ወይም በልባቸው ውስጥ አሁንም የተደበቀውን መበላሸትና አታላይነትን ለማሳየት ነው። ስለዚህም እነሱ ትሁታን በመሆን ተነስተው በጣም ወደቀ ረበና ወደማያቋርጥ በእሱ ላይ መታመን፣ ለእርዳታ ወደ እሱ እንዲመጡ ነው። እንዲሁም ለወደፊት የኃጢአት መከሰት የበለጠ ጥንቁቅ እንዲሆኑ ነው። ሌሎችም ትክክልና ቅዱስ የሆኑ ዓላማዎቹም እንዲሁ በእግዚአብሔ ር ለእንዲህ ዓይነት ተግባራት ያገለግላሉ[15]።

ስለዚህም ለምርጦቹ የሚሆነው ማንኛውም ነገር በእሱ ዕቅድና ለእሱ ክብር እንዲሁም ለእነሱ ጥቅም ነው የሚሆነው[16]።

15. 2ዜና 32:25-31፣ 2ዜና 12:7-9፣ 16. ሮሜ 8:28።

6. ኃጢአተኞች ለሆኑትና እግዚአብሔራዊ ላልሆኑት ሰዎች እግዚአብሔር እንደ ፃድቅ ዳኛ (ፈራጅ) ለሆናቸው፣ ላለፈው ኃጢአታቸው

ሊሰበን፣ ሊደግፈን፣ ሊያድነን፣ እንዲሁም ወደ እሱ ሰማያዊ መንግሥት እስከንደርስ ድረስ ሊያፀናን የእሱ ንጉሥነት ያስፈልገናል[46]፡፡

44. ዮሐ. 1:18፣ 45. ቆላ. 1:21፣ ገላ. 5:17፣ 46. ዮሐ. 16:8፣ መዝ. 110:3፣ ሉቃ. 1:74-75፡፡

# ፱. ነፃ ፈቃድ

1. የሰውን ፈቃድ በተፈጥሮ፣ በነፃነት እና በመምረጥ ኃይል እንዲሁም በምርጫው ላይ ተግባራዊ ማድረግ የሚችል ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር አለበሰው (ለስታጠቀው)፡፡ ይህ ነፃ ፈቃድ መልካምን ለማድረግ ወይንም ክፉ በግዳጅ ያልሆነ ወይም በማንኛውም የተፈጥሮ አስፈላጊነት ያልተወሰነ ነው[1] (በውስጥ የተገነባ ግዳጅ የለውም)፡፡

1. ማቴ. 17:12፤ ያዕ. 1:14፤ ዘዳ. 30:19፡፡

2. ሰው በእሱ (የመጀመሪያ) ንፁህነት ሁኔታ፤ እግዚአብሔርን በሚገባ የሚያስደስተውንና[2] መልካም የሆነውን ለማድረግ ነፃነትና ኃይል ነበረው ነገር ግን እሱ የፀና አልነበረም፤ ስለዚህም ከዚህ ሁኔታ ሊወድቅ ይችል ነበር[3] (ሙሉ ነፃነት ያስጥርጥር የሚጨምረው ያስመርጋትን ቁዐፍ ነገር ነው - ይህም ሳስመታዘዝ ከመረጠ የመውደቅ ነፃነት ነበር ማስት ነው)፡፡

2. መክብ. 7:29፤ 3. ዘፍጥ. 3:6፡፡

3. ሰው በኃጢአት ሁኔታ ውስጥ በመውደቁ ከደኅንነት ጋር ሊሄድ የሚችለውን ማንኛውንም መንፈሳዊ መልካም ነገር የማድረግን ፈቃድና ችሎታ ሙሉ በሙሉ ጥሏል[4]፡፡ እንደ ፍጥረታዊ ሰው (የመንፈሳዊ ሰው ተቃራኒ) እሱ በአጠቃላይ ለመንፈሳዊ መልካም ነገር ሁሉ ተቃራኒ ሆኗል፤ እናም በኃጢአት ሞቷል[5]፡፡ ስለዚህም በራሱ ኃይል ራሱን ሊለውጥ አይችልም ወይም ለመለወጥ ራሱንም ሊያዘጋጅ አይችልም[6] (ይህንን ለመናፈቅም ለመፈለግም እንኳን ቢሆን)፡፡

4. ሮሜ 5:6፣ ሮሜ 8:7፣ 5. ኤፌ. 2:1-5፣ 6. ቲቶ 3:3-5፣ ዮሐ. 6:44፡፡

4. እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በሚለውጥበት እና በፀጋ ሁኔታ ውስጥ በሚቀይርበት ጊዜ (የሚያሳየው) ኃጢአትን ከማድረግ የተፈጥሮ እስራቱ ይፈታዋል[7] እንዲሁም በፀጋው ብቻ መንፈሳዊ መልካም የሆነውን ነገር

አይደለም:: በዚህ ጉዳይ በፍፁም ተሳታፊ ባልሆነው በፍጡሩ ውስጥ፣[7] በሌላ በምንም ኃይል ወይም ወኪል በኩል (ብቃት ወይም ሥራ) የተነሳ አልተደረገም:: ስለዚህም በመንፈስ ቅዱስ እስከሚነቃና እስኪታደስ ድረስ (ሕይወት እስከሚያገኝ) ሰው በኃጢአቱና በመተላለፉ የሞተ ነው[8]:: በዚህ ብቁ የተ ጥሪ፣ ጥሪውን ለመቀበል እንዲችል ይደረጋል እንዲሁም በዚህ ላለፈለትንና የቀረበለትን ፀጋ እንዲይዝ ይደረጋል:: ይህ የሚያስችል ኃይል ክርስቶስን ከሞት ካስነሳው ኃይል ያነሰ ኃይል አይደለም[9]::

7. 2ጢሞ. 1:9፣ ኤፌ. 2:8፣ 8. 1ቆሮ. 2:14፣ ኤፌ. 2:5፣ ዮሐ. 5:25፣
9. ኤፌ. 1:19-20::

3. በህፃንነታቸው የሚሞቱ ህፃናት በመንፈስ ቅዱስ[10] በኩል ዳግም ተ ወልደው በክርስቶስ ድነዋል ይህም መቼ፣ የት፣ እንዴት እንደሚሠራ በሚያስደስተው በእሱ የተደረገ ነው[11]:: በውጪ በሚደረግ በቃሉ ጥሪ ለመጠራት በማይችሉት ለተመረጡ ሰዎችም ሁሉ ልክ እንደዚሁ ነው::

10. ዮሐ. 3:3-6፣ 11. ዮሐ. 3:8::

4. ሌሎች አልተመረጡም፣ ምንም በቃሉ አገልግሎት ቢጠሩም እንኳን እንዲሁም አንዳንድ የመንፈስን አጠቃላይ[12] (የጋራ) አሠራር ልምምድ (የተወሰነ መረዳትና ኃጢአተኝነትን ማወቅ) ሆኖም ገና በአብ በብቁ ቢለማመዱም ጥሪው ስላልተሳቡ ወደ ክርስቶስ በእውነት ሊመጡ አይችሉም፣ አይመጡምም ስለዚህም ሊድኑ አይችሉም[13]:: ብዙ ሰዎች በተፈጥሮ ዕ ውቀት አማካኝነት ሕይወታቸውን ለመምራት ምንም ያህል ትሁታን ቢሆኑና (በተፈጥሮ መረዳታቸው) የሚያምኑበት ሃይማኖታቸውም የሚያዘውን ምንም ያህል ቢፈፅሙ፣ የክርስትናን (የደኅንነትን) እምነት (በጌታ ቃል መሠ ረት) ካልተቀበሉ ሊድኑ አይችሉም[14]::

12. ማቴ. 22:14፣ ማቴ. 13:20-21፣ ዕብ. 6:4-5፣ 13. ዮሐ. 6:44-45 እና 65
1ዮሐ. 2:24-25፣ 14. ሐዋ. 4:12፣ ዮሐ. 4:22፣ ዮሐ. 17:3::

## 11. ፅድቅ

1. እግዚአብሔር በብቁ ጥሪው የጠራቸውን እነዚያን ደግሞ በነፃ አፅድቆአቸዋል[1]፣ ይህም በእነሱ ውስጥ ፅድቅን በማስገባት አይደለም:: ነገር ግን ኃጢአታቸውን ይቅር በማለትና እነሱን እንደፃድቅ በመቁጠርና

4. ከዘላለም በፊት እግዚአብሔር የደነገገው (የወሰነው፣ ያወጀው) የተመረጡትን ሁሉ ለማፅደቅ ነው[11]:: ስለዚህም ጊዜው ሲደርስ ክርስቶስ ስለኃጢአታቸው ሞቶ ለፅድቃቸው እንደገና እንዲነሳ ነው[12]:: ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን በሕይወታቸው እስኪገልፀው ድረስ እስከዚያን ጊዜ ድረስ በግላቸው ሊፀድቁ አይችሉም[13]::

11. ገላ. 3:8፣ 1ጴጥ. 1:2፣ 1ጢሞ. 2:6፣ 12. ሮሜ 4:25፣ 13. ቆላ. 1:21-22፣ ቲቶ. 3:4-7::

5. እግዚአብሔር የእነዚያን የፀደቁትን[14] ኃጢአት ይቅር ማለቱን ይቀጥላል:: አማኞች ከፅድቅ ሁኔታ ምንም እንኳን በፍፁም ሊወድቁ ባይችሉም[15] ነገር ግን በኃጢአታቸው የተነሳ በእግዚአብሔር አባታዊ ቅሬታ ሥር ይወድቃሉ[16]:: በዚያን ሁኔታ ኃጢአታቸውን እስካልተናዘዙና ዝቅ ብለው በትህትና በመቅረብ ይቅርታን እስካልጠየቁ ድረስና እምነታቸውን እስካላደሱ (ቀጣይ የእምነት እርምጃ) ድረስ የእግዚአብሔር የፊቱ ብርሃን ለእነሱ ብዙውን ጊዜ አይታይላቸውም[17]::

14. ማቴ. 6:12፣ 1ዮሐ. 1:7-9፣ 15. ዮሐ. 10:28፣ 16. መዝ. 89:31-33፣ 17. መዝ. 32:5፣ መዝ. 51፣ ማቴ. 26:75::

6. በብሉይ ኪዳን ጊዜም ውስጥ የነበረው የአማኞች መፅደቅ በማንኛውም መልኩ ቢሆን በአዲስ ኪዳን ካለው የአማኞች ፅድቅ ጋር ይመሳሰላል[18]::

18. ገላ. 3:9፣ ሮሜ 4:22-24::

## 12. ልጅነት

በክርስቶስ በአንድ ልጁ እናም በእሱ አማካኝነት የፀደቁ ሁሉ የፀጋ ልጅነት ተካፋዮች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ፈቅዷል[1] (ዋስትና ሰጥቷል) ይህም ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ቁጥር ውስጥ ገብተው ነፃነታቸውንና መብታቸውን እንዲደሰቱበት ነው[2]:: በነሱ ላይ የተደረገው ስሙ አላቸው[3] እንደዚሁም የልጅነትን መንፈስ ተቀብለዋል[4]:: በድፍረት ወደ ፀጋው ዙፋን የመግባት መብትና «አባ አባት»[5] ብለው ለመጮህ ችለዋል:: ታዝኖላቸዋል[6] (እንክብካቤና የርኅራኄ ፍቅር ሰጥተዋል) ተጠብቀዋል[7]፣

3. ከዚህ በአጠቃላይ የሞራል ሕግ ከሚባለው ሕግ ባሻገር የተለያዩ ብዙ ምስያዊ ሥርዓቶችን ያካተቱ የሥርዓት (Ceremonial Laws) ሕጎችን ለእስራኤላውያን ለመስጠት እግዚአብሔር ደስ ተሰኘ፣ (ምሳሌያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ከራሳቸው ውጪ ሌላ ነገርን የሚያመለክቱ ሥርዓቶች):: እነዚህ ሥርዓቶች በከፊል ስለ አምልኮአቸው የነበሩ ሲሆን በእነሱም ውስጥ ክርስቶስ ከባሕርያቱ፣ ከሃላፊነቱ እንዲሁም ከተግባሩ ከስቃዩ እና ከጠቀሜታዎቹ[6] ጋር በቅድሚያ ተመስሎ (ጴታጴ ነበር) ነበር:: በተጨማሪ እነዚህ ሥርዓቶች ስለተለያዩ የሞራል ተግባራትም መመሪያን ሰጥተዋል[7]::

እነዚህ ሥርዓታዊ ሕግጋት በሙሉ እስከመታደስ ዘመን ድረስ ብቻ እንዲያገለግሉ ተመድበው ነበር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው መሲህ እና ብቸኛው ሕግ ሰጪና ለዚህ ተግባር ከአብ ዘንድ በሥልጣን (በኃይል) የተሞላው ሻራቸው እንዲሁም ከመንገድ አስወገዳቸው[8]::

6. ዕብ. 10:1፣ ቆላ. 2:17፣ 7. 1ቆሮ. 5:7፣ 8. ቆላ. 2:14-17፣ ኤፌ. 2:14-16::

4. ለእስራኤል ሕዝብ ልዩ ልዩ ፍትሐዊ ሕግጋትን ሰጣቸው ይህም አንድ ሕዝብ (መንግሥት) መሆናቸው ሲያበቃ ጠፍቷል:: እነዚህም የዚያ ሕዝብ ሕግ ከመሆናቸው የተነሳ በማንም ላይ አይሠሩም ነገር ግን የእነሱ አጠቃላይ ትክክለኛነት በዚህም ዘመናዊው ዓለም ውስጥ ተግባራዊ መሆኑ ቀጥሏል (የእነሱ ፍትሐዊነትና ትክክለኛነት መሠረታዊ መርሆዎች)[9]::

9. 1ቆሮ. 9:8-10::

5. የሞራል ሕጉ ማናቸውም ሰው ይታዘዘው ዘንድ ያስገድዳል የፀደቁትንም ሰዎች ሆነ ሌሎችንም[10] ይህም በውስጣቸው ያለውን ከማክበር የተነሳ ብቻ ሳይሆን ሕጎቹን ለሰጠው ፈጣሪ ሥልጣን ክብር መስጠት የተነሳ ጭምር መሆን አለበት[11]:: ክርስቶስም እነዚህን ሕግጋት በወንጌል ውስጥ በምንም መንገድ አላፈረሳቸውም ነገር ግን (በስንፃሬ) እሱ እነሱን እንድንታዘዝ በሚገባ ሁኔታ ግዴታችንን አጠናከረው እንጂ[12]::

10. ሮሜ 13:8-10፣ ያዕቆ. 2:8-12፣ 11. ያዕቆ. 2:10-11፣ 12. ማቴ. 5:17-19፣ ሮሜ 3:31::

6. ምንም እንኳን እውነተኛ አማኞች ለመፅደቅና ለመኮነን በሥራዎች ቃል-ኪዳን ሕግ ሥር ባይሆኑም[13]፣ ነገር ግን ለእነሱም ለሌሎቹም ታላቅ ጠቀሜታ አለው ምክንያቱም እንደ የሕይወት ሕግ የእግዚአብሔርን ፈቃድና የእራሳቸውን ተግባር ይጠቁማቸዋል እንደዚሁም በዚያ መሠረት እንደሚገባ እንዲመላለሱ ያዛቸዋል::

በመረዎቻቸው ላይ (ተፅዕኖ) ሊጭኑ አይችሉም[30]::

29. ሐዋ. 15:2-6፣ 22-25 30. 2ቆሮ. 1:24፣ 1ዮሐ. 4:1::

# ፳፯. የቅዱሳን ኅብረት

## (የቅዱሳን ኅብረትና አብሮ መከፋፈል)

1. እራሳቸው ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆኑት ቅዱሳን ሁሉ፣ በመንፈስ እና በእምነት እነሱ በእዚህ ሁሉ ከእሱ ጋር አንድ ሰው ባይደ ረጉም በእሱ ፀጋዎች፣ ሥቃዮች፣ ሞት፣ ትንሣኤ እና ክብር ኅብረት አላቸው[1]:: (ከእነዚህ ሁሉ እውነተኛ ጥቅሞችን በመቀበል ዘላለማዊ ደስታን ይደሰታሉ)::

እንዲሁም እርስ በእርስ በፍቅር አንድ ሆነው በእያንዳንዳቸው ፀጋና ስጦታዎች ሕብረት አላቸው[2]:: እንዲሁም ለእንደዚህ ዓይነት ሥርዓታዊ የአደባባይና የግል ክንዋኔዎች (በማረጋገጫ ጥቅሶች ላይ የተጠቀሱት አገልግሎቶች) ለውጪውና ለውስጡም ሰው ለጋራ መልካም (ፍሬ) በአግባቡ እንዲመራ የማድረግ ግዴታ አለባቸው[3] (በሥጋና በመንፈስ)::

(ሥርዓታዊ እዚህ ያለው በ1ተሰ. 5:14 ላይ ያሉትን «ሥርዓት አልበኞች» የሆኑትን ሰ ዎች ስለመጥቀስ ነው:: ሁሉም በሚገባ በሚመራ ኅብረት ውስጥ ነው መደረግ ያለበት)::

1. 1ዮሐ. 1:3፣ ዮሐ. 1:16፣ ፊሊ. 3:10፣ ሮሜ 6:5-6፣ 2. ኤፌ. 4:15-16፣ 1ቆሮ. 12:7፣ 3:21-23፣ 3. 1ተሰ. 5:11፣ ሮሜ 1:12፣ 1ዮሐ. 3:17-18፣ ገላ. 6:10::

2. ቅዱሳን በእምነት ቃላቸው (ያም ለክርስቶስና ለመንግሥቱ የተሰጡ ስለሆኑ) እግዚአብሔርን ለማምለክ ቅዱስ ኅብረትና አንድነትን ለመጠበቅና እንደዚህ ዓይነት መንፈሳዊ አገልግሎቶችን (መንፈሳዊ ጥቅም) ለማከናወን የጋራ መተናነፃቸውን ለማሳደግ ተያይዘዋል[4]:: እንዲሁም በውጪያዊ ጉዳዮች፣ እነሱን ለማሟላት እንዳላቸው የተለያየ ፍላጎትና ችሎታ ለእርስ በእርስ እርዳታን መስጠት አለባቸው (ሕመምን ጭንቀትን ወይም ችግርን ለማቃለል)[5]::

ይህ አንድነት ወይም ኅብረት በቀረቤታቸው ባሉ በቅዱሳን አማኞችና ቤተሰቦች[6] እና ቤተክርስትያናት[7] በዋናነት የሚደረግ ቢሆንም (በወንጌል ትዕዛዝ መሠረት) እግዚአብሔር ዕድልን እንደሰጠን መጠን ለአማኞች ቤተ ሰቦች ሁሉ መስፋፋት አለበት:: ይህም በየቦታው የጌታን የኢየሱስን ስም

ለሚጠሩት ሁሉ ነው፡፡ ቢሆንም እንደ ቅዱሳን ከእያንዳንዳቸው ጋር ያላቸው አንድነት፣ በግል እያንዳንዱ ሰው ያለውን የግል ንብረት ወይም የራስ ነገር አይወስድም ወይም አይጥስም[8]፡፡

4. ዕብ. 10:24-25፣ ዕብ. 3:12-13፣ 5. ሐዋ. 11:29-30፣ 6. ኤፌ. 6:4፣
7. 1ቆሮ. 12:14-27፣ 8. ሐዋ. 5:4፣ ኤፌ. 4:28፡፡

# ፳፰. ጥምቀትና የጌታ እራት

1. ጥምቀትና የጌታ እራት በመለኮት የተቋቋሙና በብቸኛው ሕግ ሰጪ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዓለም ፍፃሜ በቤተክርስትያኑ እንዲቀጥሉ የተመደቡ አዎንታዊና መለኮታዊ ተቋማት፤ ሥርዓቶች ናቸው[1]፡፡ (አዎንታዊ እዚህ ጋ የሚያሳየው እነዚህ ሥርዓቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሳቸውን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በትክክል እና በአዎንታዊ መልኩ የታዘዙ መሆናቸውን ነው፡፡ እነሱ በክርስቶስ በግልፅ የተመሠረቱ ናቸው)፡፡

1. ማቴ. 28:19-20፣ 1ቆሮ. 11:26፡፡

2. እነዚህ ቅዱሳን ሥርዓቶች መከናወን ያለባቸው እነዚህን ለማከናወን ብቃት ባላቸውና፤ በክርስቶስ ሹመት ምክንያት ለዚህ በተጠሩት ነው[2]፡፡

2. ማቴ. 28:19 1ቆሮ. 4:1፡፡

# ፳፱. ጥምቀት

1. ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ የታዘዘ የአዲስ ኪዳን ሥርዓት ሲሆን፣ ለሚጠመቀውም ሰው ከክርስቶስ ጋር በሞቱና በትንሳኤው እንዲሁም በክርስቶስ ውስጥ ለመጣበቁ የመተባበር ምልክት ነው[1]፡፡ ለኃጢአቱ መሠረይ[2] እናም ያ ሰው በክርስቶስ በኩል በአዲስነት ሕይወት ለመኖርና ለመመላለስ እራሱን ለእግዚአብሔር መስጠቱን የሚያሳይ ነው[3]፡፡

1. ሮሜ. 6:3-5፣ ቆላ. 2:12፣ ገላ. 3:27፣ 2. ማር. 1:4፣ ሐዋ. 22:16፣ 3. ሮሜ. 6:4፡፡

2. ለዚህ ሥርዓት የሚበቁት[4] (መብት ያላቸው)፣ እነዚያ ወደ እግዚአብሔ

ር ንስሐን የገቡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑና ለእሱም የሚታዘዙ ብቻ ናቸው::

4. ማር. 16:16፣ ሐዋ. 8:36-37፣ ሐዋ. 2:41፣ ሐዋ. 8:12፣ ሐዋ. 18:8::

3. በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሰውየው በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ለሚጠመቅበት ጥቅም ላይ የሚውለው ውጫዊው መጠቀሚያ ውሃ ነው[5]::

5. ማቴ. 28:19-20፣ ሐዋ. 8:38::

4. መጥለቅ - የሰውየው በውሃ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መግባት - ለዚህ ሥርዓት በትክክል መከናወን አስፈላጊ ነው[6]::

6. ማቴ. 3:16፣ ዮሐ. 3:23::

# ፴. የጌታ እራት

1. የጌታ የኢየሱስ እራት እሱ በተከዳበት፤ አልፎ በተሰጠበት ምሽት በእራሱ የተመሠረተ ነው:: ይህም በቤተክርስትያን ውስጥ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ለሁልጊዜ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ እንዲደረግና እንዲሁም እሱ እራሱ በሞቱ ያደረገውን መስዋዕትነት እንዲያሳይ ነው[1]:: በክርስቶስ የተመሠረተው ለአማኞች የሞቱን ጥቅም ሁሉ ለማሳየትም ጭምር ነበር:-

- ለመንፈሳዊ ምግባቸውና በእሱ እንዲያድጉ::
- ለእሱ በሚመራቸው ተግባር ሥራ ሁሉ ላይ ያላቸውን እንቅስቃሴና መሰጠታቸውን እንዲቀጥሉ::
- እንዲሁም ከእርሱ ጋርና አብረዋቸው ካሉ አማኞች ጋር ላላቸው ለአንድነታቸው ጥንካሬ ትስስርና ቃልኪዳን እንዲሆን[2] ነው::

1. 1ቆሮ. 11:23-26፣ 2. 1ቆሮ. 10-16-21::

2. በዚህ ሥርዓት ክርስቶስ ለአብ «እንደ መስዋዕት» በመሆን አይሰጥም እንዲሁም ምንም ዓይነት ለኃጢአት ማስተሰርያ የሚሆን እውነተኛ መስዋዕት አይቀርብም (በሕይወት ሳሉትም ለሞቱትም):: የሚደረገው ነገር፤ ክርስቶስ ራሱን እንዴና ለመጨረሻ በመስቀል ላይ ለሰጠለት ለዚያ አንድ መስዋዕትነት መታሰቢያ ብቻ ነው[3]:: መታሰቢያውም፤ ስለቀራንዮው መስቀል ለእግዚአብሔር ሊቀርብ ከሚቻለው የመንፈሳዊ ምስጋና ስጦታ

(መስዋዕት) ሁሉ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት[4]::

ስለዚህም ጳጳሳዊው (የሮማን ካቶሊክ) የቁርባን መስዋዕት (እነሱ እንደሚጠሩት) በጣም አስከፊ ነው (በመንፈሳዊውም በሥጋዊውም መዕኩ ለስፀያፊ ነው):: ለተመረጡት ሁሉ ኃጢአት ብቸኛ የኃጢአት ማስተሰርያ (ምህረት ማግኛ፣ ለስታሬቂ) የሆነውን የክርስቶስን የራሱን መስዋዕትነት የሚያዋርድ ነው::

3. ዕብ. 9:25-28፣ 4. 1ቆሮ. 11:24፣ ማቴ. 26:26-27::

3. በዚህ ሥርዓት ውስጥ አገልጋዮቹ እንዲፀልዩ እና ወይኑንና ዳቦውን እንዲባርኩ ጌታ ኢየሱስ ሾሟቸዋል፣ (ስለዚህም እነሱን ከተራ ወደ ቅዱስ ለጠቃቀም ለይቷቸዋል):: እናም ዳቦውን ለመውሰድና ለመቁረስ ከዚያም ፅዋውን ለመውሰድ እናም ሁለቱንም ለተሳታፊዎቹ ለመስጠት እንዲሁም እራሳቸው ሊሳተፉበት[5] ነው::

5. 1ቆሮ. 11:23-26::

4. ፅዋውን ለሕዝቡ መከልከል፣ ዳቦውንና ወይኑን የማምለክ ልምምድ፣ እነሱን ወደ ሰማይ ከፍ ማድረግ ወይም በማክበር ከፍ አድርጎ መሸከም ወይም ለማንኛውም ሃይማኖታዊ መሰል አገልግሎት ለመጠቀም እነሱን ማስቀመጥ፣ እነዚህ ሁሉ ከሥርዓቱ ባህርይ (ለናም ከትርጉሙ) እንዲሁም ክርስቶስ ከመሠረተው ተቋም[6] ጋር በጣም የተቃረኑ ናቸው ::

6. ማቴ. 26:26-28፣ ማቴ. 15:9፣ ዘፀ. 20:4-5::

5. ክርስቶስ እንዳዘዘው በዚህ ሥርዓት ውስጥ ያሉት ውጫዊ መጠቀሚያ ነገሮች በትክክል የተቀመጡት እና ጥቅም ላይ የዋሉት እሱን እንደተሰቀለ በደምብ አድርገው በመመሰል ነው:: ያም እነሱ አንዳንድ ጊዜ በእውነት (ግን በምሳሌነት) የሚወክሉትን ነገር ያመለክታሉ፣ ይህም እንደ ክርስቶስ አካልና ደም[7] ነው:: ይሁን እንጂ (እነዚህ ቃላት በትክክል ለወይኑና ለዳቦው ቢውሉም) በተፈጥሮአቸውና በይዘታቸው እነሱ በእውነት ከዚህ በፊት እንደነበሩት ሁሉ አሁንም ዳቦና ወይን ብቻ ናቸው[8]::

7. 1ቆሮ. 11:27፣ 8. 1ቆሮ. 11:26-28::

6. ዳቦውና ወይኑ በካህኑ ሲባረኩ ወይም በሌላ መንገድ፣ በዳቦውና በወይኑ ተፈጥሮ ላይ ለውጥ ይከናወንና ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደምነት ይቀየራሉ የሚለውን ዶክትሪን፣ በተለምዶ «መቀየር» (ትራንስበስታንሼሽን) በመባል የሚታወቀው፣ (ትምህርትና እምነት) የማይስማማው

ስጣቸው ወደ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ትመለሳለች[2]::

ከዚያም የፃድቃን ነፍሶች በቅድስና ፍፁማን ይደረጋሉ ከክርስቶስ ጋር ወደሚሆኑበት ወደ ገነት ተቀባይነት ያገኛሉ:: እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፊት በክብርና በብርሃን ያያሉ፣ እንዲሁም የሙሉ የአካላቸውን ደኅንነት ይጠባበቃሉ[3]::

የኃጢአተኞች ነፍሶች ለታላቁ የፍርድ ቀን ተጠብቀው በሚቆዩበት በሥቃይና በጭለማ ሥፍራ ወደ ሲዖል ይጣላሉ[4]:: መጽሐፍ ቅዱስ ከሥጋቸው ለተለዩ ነፍሶች ከነዚህ ከሁለቱ ቦታዎች ወይም ሁኔታዎች ስለሌላ ቦታ አያውቅም::

1. ዘፍ. 3:19፣ ሐዋ. 13:36፣ 2. መክብ. 12:7፣ 3. ሉቃ. 23:43፣ 2ቆሮ. 5:1 እና 6-8፣ ፊሊ. 1:23፣ ዕብ. 12:23፣ 4. ይሁዳ 6-7፣ 1ጴጥ. 3:19፣ ሉቃ. 16:23-24::

2. በመጨረሻው ቀን በሕይወት ያሉት እነዚያ ቅዱሳን አያንቀላፉም (አይሞቱም) ነገር ግን ይለወጣሉ[5]:: እንዲሁም የሞቱት ሁሉ ከራሳቸው አካል ጋር ሌላ ሳይሆን እራሳቸውን ሆነው ይነሳሉ[6] ሆኖም በተለየ ዓይነት ሁኔታ ነው እነዚህም አካላት ከራሳቸው ነፍሶች ጋር ለዘላለም ይዋሃዳሉ[7]::

5. 1ቆሮ. 15:51-52፣ 1ተሰ. 4:17፣ 6. ኢዮብ. 19:26-27፣ 7. 1ቆሮ. 15:42-43::

3. የኃጢአተኞች አካል በክርስቶስ ኃይል ለውርደት ይነሳሉ:: የፃድቃን አካላት በመንፈሱ ለክብር ይነሳሉ እናም የእሱን የከበረ አካል እንዲመስሉ ይለወጣሉ[8] (ይቀየራሉ፣ እንደገና ይሠራሉ፣ ተመሳሳይ ይሆናሉ)::

8. ሐዋ. 24:15፣ ዮሐ. 5:28-29፣ ፊሊ. 3:21::

# 32. የመጨረሻው ፍርድ

1. እግዚአብሔር ዓለምን በዕድቅ የሚፈርድበትን ቀን መድቧል:: ይህም በአብ ኃይልና ፍርድ ሁሉ (የፍርድ ሥልጣን ሁሉ) በተሰጠው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው[1]:: በዚህ ዕለት የሚፈረድባቸው ያጠፉት መላዕክት ብቻ ሳይሆኑ ነገር ግን በምድር ላይ የኖሩ ሰዎች ሁሉ ናቸው[2]:: እነሱ በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ይቀርቡና ስለራሳቸው ሐሳብ፣ ስለቃላቸው እና ሥራቸው ይናገራሉ በአካል በነበሩበት ጊዜ መልካምም ይሁን መጥፎ ያደረጉት እንደሥራቸው መጠን (ፍርድን) ይቀበላሉ[3]::

## ዊክማን ትረስት በአማርኛ የታተሙ ሌሎች መጽሐፍት

### ሁሉ ከንቱ ትርጉመ ቢስ

ንጉሱ ሰለሞን ደስታን ሊሰጡ ይችላሉ የሚባሉትን ነገሮች ሁሉ ከፈተነና ከመረመረ እንዲሁም ካየ በኋላ ሁሉ ነገር ከንቱና ትርጉም የለሽ መሆኑን ተረድቷል:: ስለዚህም ሰዎች ጌታን ፈልገው ካላገኙ እንዲሁም በሕይወታቸው የጌታን ምህረት ኃይሉንና ምሪቱን ካልተለማመዱ በስተቀር ሁሉ ነገር የተለመደና ጥቅም የሌለው እንዲሁም ትርጉመ ቢስ መሆኑን ተናግሯል:: በዚህ እውነታ ላይ በመመሥረት ይቺ መጽሐፍ ሰ ዎች ሁሉ በጊዜ ወደ ጌታ እንዲመለሱ ታሳስባለች::

### የእውነተኛ መለወጥ ሰባቱ እርግጠኛ ምልክቶች

በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ እርግጠኛ መለወጥ መከናወኑን እንዲሁም ያ ሰው በእርግጥ በጌታ መሆኑን ለማወቅ የሚጠቅሙ የሕይወት ለውጥ ማስረጃዎች ይኖራሉን? አንድ ሰው መለወጡን እንዴት እናውቃለን? ይቺ ትንሽ መጽሐፍ መለወጣቸውን በመጠራጠር ለሚቸገሩና እነሱንም ለመርዳት በማማከር ለሚያገለግሉ መምሪያነት የምትጠቅም ናት::

### የቤተ ክርስትያን አባልነት

በጌታ ተለውጦ የቤተክርስትያን አባል የሆነው አማኝ በቤተክርስትያን ውስጥ ድርሻው ምንድነው? የቤተክርስትያን አባልነትስ ምን ማለት ነው? አባላት ሊታዘዙት የሚገባቸው የሥነ ምግባር ግዴታ አለባቸውን? የአባላት ምንነት ከቤተክርስትያን ምንነት ጋር የተያያዘና የተጣመረ ነው:: ይህንን የምትገልጠውን ይህችን መጽሐፍ መመልከት ስለቤተክርስትያን አባልነት ሊኖረን የሚገባውን አዲስ ኪዳናዊ ግንዛቤ ይሰጠንና በጌታ ቤት ውስጥ ትክክለኛ የአባልነት ድርሻችንን ለመወጣት እንድንችል ያደርገናል::

### የነፍሶች ሐኪሞች

#### የወንጌል አገልግሎት

በአሁኑ ጊዜ ኃጢአተኝነትን አሳምኖ የእግዚአብሔርን ምህረትና ማዳን ለሞቱት ነፍሳት የሚገልጥ ስብከት ብዙ አይሰማም:: በመሆኑም በኃጢአት ለወደቅነው ለእኛ ለሰው ልጆች ከተሰጡን ሁሉ እጅግ የላቀው ጥበብ ጠፍቷል ለማለት ይቻላል:: ስለዚህም ጸሐፊው ለአሳማኝ የወንጌል ስብከት የሚያገለግሉ ጥቅሶች እንዴት እንደሚመረጡና እንደሚዘጋጁ ያሳያል:: ከዚህም በተጨማሪ የዘመናዊውን የቤተክርስትያን ዕድገትን እንቅስቃሴዎች ሥጋዊ ቴክኒኮችን እየነቀፈ ከሁሉ የሚበልጠውን ታላቅና ቀጥተኛ የወንጌል ስብከት አገልግሎትን ጠቀሜታ ያብራራል::

### ዕድቅ ፈላጊው ኢትዮጵያዊ

#### መንገዱን ደስ ብሎት ሄደ

ለወንጌል ስርጭት አገልግሎት የምታገለግልና በሐዋርያት 8:26-40 ባለው ጥቅስ ላይ የተመሠረተች ትራክት ናት:: በእውነት ጌታን እና የዕድቅ መንገዱን ለማወቅ ለሚጠሙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የዕድቅን መንገድ ማግኛውን እውነትና መንገድ የምትጠቁም ናት::

## በቅርብ የሚታተሙ መጽሐፍት

## የሰንበት ትምህርት ቤትን ጀምሮ ማሳደግ

የሚመጣውን ትውልድ በእግዚአብሔር ቃል እውነት አሳድጎ የጌታን መንገድ ተከታይ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚረዳ መመሪያ ነው:: ይህ ተግባራዊ መመሪያ አንድ የሰንበት ትምህርት ቤትን እንዴት መጀመር መምራትና አሳድጎም ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ያስረዳል::

## ትምህርት ለሕይወት

የአራት ዓመት ተከታታይ የሰንበት ትምህርት መጽሐፍት (መጽሐፍ 1-4):: በአራት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ የሚሰጡና ወንጌል ተኮር በመሆን በአስደናቂ ሁኔታ የተዘጋጁ ተከታታይ የሰንበት ትምህርት መጽሐፍት ናቸው::

